ለአዲስ የSNAP EBT ቺፕ ካርዶች ሱቅዎን አሁኑኑ ያዘጋጁ



ሁሉም በSNAP ለመገበያየት ፈቃድ ያላቸው ቸርቻሪዎች የEMV ቺፕ ካርዶችን መቀበል አለባቸው።

ቨርጂኒያ የደንበኞችን ጥቅማጥቅሞች ለመጠበቅ የSNAP EBT ካርዶችን፣ ደህንነቱ በተጠበቀ የEMV ቺፕ ካርድ በመተካት እያዘመነች ነው። የመደብር መውጫ ላይ የሚሰሩ ሰራተኞችዎ ምን መጠበቅ እንዳለባቸው እና ደንበኞችን አዲሶቹን ካርዶች በመጠቀም ላይ ያሉ ደንበኞችን እንዴት መርዳት እንደሚችሉ እንደሚያውቁ ያረጋግጡ።

1

በሴፕቴምበር ወር መጀመሪያ ላይ
ቸርቻሪዎች አዲስ የSNAP EBT ቺፕ ካርዶችን ለመቀበል ዝግጁ መሆን አለባቸው። ይህ የሱቅዎን POS ስርዓት ማዘመን ወይም ማሻሻል ሊጠይቅ ይችላል።

2

በሴፕቴምበር ወር አጋማሽ ላይ
በተመረጡ የሙከራ አከባቢዎች የሚገኙ የSNAP ደንበኞች ቺፕ ያላቸው ካርዶችን የሚያገኙ ሲሆን፣ ወዲያውኑ ስራ እንዲያስጀምሩ ይበረታታሉ።

3

ኦክቶበር - ዲሰምበር
በመላው ቨርጂኒያ ያሉ የSNAP ደንበኞች አዲስ ቺፕ ያላቸውን ካርዶች ይቀበላሉ።

4

ዲሰምበር 31 ቀን 2026
ሁሉም በቨርጂኒያ ውስጥ ያሉ የSNAP ደንበኞች አዲስ ቺፕ ያላቸው ካርዶችን ተቀብለዋል።

ማስታወሻዎች፡-

- አዲስ ካርዶች ደንበኛው ጋር ሲደርሱ ወዲያው ስራ እንዲጀምሩ መደረግ አለባቸው።
- አዲሱ ካርድ ስራ እንዲጀመር ከተደርገ በኋላ ወዲያው ወይም አዲሱ ካርድ ከተሰጠ ከ60 ቀናት በኋላ የድሮው ካርድ መስራት ያቆማል።
- ይህ በግዛት ደረጃ ተግባራዊ የሚደረግ ዝማኔ ነው እንጂ የአንድ መደብር ውሳኔ አይደለም።

አንድ ደንበኛ ካርዱን ለመጠቀም ችግር ካጋጠመው፡-

- ታጋሽ እና ደጋፊ ይሁኑ።
- አዲሱን የቨርጂኒያ SNAP EBT ካርድ ተቀብለው እንደሆነ ይጠይቁ።
- ማግኔታዊ የሆኑትን መስመሮች አንደ ሁለተኛ አማራጭ አድርገው ይጠቀሙ።

ካርድ ውድቅ ከተደረገ ወይም የማይሠራ ከሆነ ምን ማለት እንዳለባቸው፡-

"ቨርጂኒያ አዳዲስ ቺፕ ያላቸው የEBT ካርዶችን በማዘጋት ደረጃ ቀስ በቀስ እያሰራጨች ነው። ካርድዎ የማይሰራ ከሆነ አዲሱ ካርድዎን ስራ ማስጀመር ሊኖርብዎ ይችላል። እባክዎን ለእርዳታ የቨርጂኒያ የማህበራዊ አገልግሎቶች ዲፓርትመንትን (Department of Social Services (VDSS)) ያነጋግሩ።"

VIRGINIA DEPARTMENT OF SOCIAL SERVICES

ለቨርጂንያ ማህበራዊ አገልግሎቶች ዲፓርትመንት ጥያቄ አልዎት?
ኢሜል chipcard@dss.virginia.gov

በቸርቻሪዎች በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች
የቸርቻሪዎችን መመሪያ እና ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የQR ኮድን ስካን ያድርጉ።